ውሳኔ አስፈጻሚ ክፍል

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS, ROCKVILLE, MARYLAND

# Section 504 ተግባራዊ ለማድረግ

*የ የተሃድሶ ደንብ/Rehabilitation Act of 1973*

## የመመሪያ መጽሐፍ

2017–2018

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

## ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ ትምህርት እንዲሰርፅ እናደርጋለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ በኮሌጅም ሆነ በስራ ስኬታማ እንዲ(ድት) ሆን አካዴሚያዊ፣ ፈጠራዊ የችግር አፈታት፣ እና የማህበራዊ ስሜታዊ ክህሎቶች ይኖሩ(ሯ)ታል።

## ዋናው ዓላማ

ሁሉም ተማሪዎች በወደፊት ኑሮአቸው የዳበረ ህይወት እንዲኖራቸው ማዘጋጀት።

## ዋና እሴቶች

መማር
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትሃዊነት/እኩልነት


## የትምህርት ቦርድ

Mr. Michael A. Durso
President
ሚ/ር ማይክል ዱርሶ ፕሬዚደንት

Mrs. Shebra L. Evans
Vice President
ወ/ሮ. ሼብራ ኤል. ኢቫንስ ም/ፕሬዚደንት

Ms. Jeanette E. Dixon
ወ/ሮ. ዣኔት ኢ. ዲክሰን

Dr. Judith R. Docca Vice President
ዶ/ር ጁዲዝ አር. ዶካ

Mrs. Patricia B. O'Neill
ወ/ሮ. ፓትሪሻ ቢ ኦኔይል

Ms. Jill Ortman-Fouse
ወ/ሮ. ጂል ኦርትማን-ፉውዝ

Mrs. Rebecca K. Smondrowski
ወ/ሮ. ሬቤካ ኬይ. ስሞንድሮውስኪ

Mr. Matthew Post
Student Member
ሚ/ር ማቲው ፖስት የተማሪ አባል

## የት/ቤት አስተዳደር

Jack R. Smith, Ph.D.
Superintendent of Schools
ዶር. ጃክ አር. ስሚት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

Maria V. Navarro Ed.D.
ዶ/ር.ማሪያ ቪ. ናቫሮ የአካዴሚ ዋና መኮንን

Kimberly A. Statham, Ph.D.
Deputy Superintendent of
School Support and Improvement
ዶር. ኪምበርሊ ኤ. ስታታም የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

Andrew M. Zuckerman, Ed.D.
Chief Operating Officer
ዶር. አንድሩ ኤም. ዙከርማን ዋና የሥራ ሀላፊ



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# ሰክሽን 504 ተግባራዊ ለማድረግ የመመሪያ መጽሐፍ

## ማውጫ


መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ተማሪን ለ ሰክሽን 504 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

ብቁ ስለመሆን መወሰን

የ ሰክሽን 504 እቅድ ማዘጋጀት/ማዳበርብቁ ለሆኑ የ MCPS ተማሪዎች . . . . . . . 4

ሰክሽን 504 የአፈጻጸም ግምገማእና ዳግመኛ ግምገማ . . . . . . . . . . . . . . . . 6

የዲስፕሊን ሥርአቶችለ ሰክሽን 504 ተማሪዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

ተመሣሣይ/የሚዛመዱ አገልግሎቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

ወላጅ/ሞግዚትትብብር እና ተሳትፎ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

የማከናወኛ ሥርአት ቅደምተከተሎች ለሰክሽን 504 ተማሪዎች . . . . . . . . . . . . 9

ተጨማሪ ጥያቄለመጠቀሚያ/Resources . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9


## አባሪዎች


የቃላት መፍቻ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

MCPS ሰክሽን 504 ቅጾች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .11

MCPS ደንብ እና ደጋፊ ሰነዶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .11

MCPS ሰክሽን 504 መገልገያዎች/Resources . . . . . . . . . . . . . . . . . . .11


## እውቅና መስጠት


ይህንን መመሪያ በማዳበር የረዱንን የ MCPS ሠራተኞች እና የት/ቤቶቻችን የጤና አገልግሎት አጋሮቻችንን ስለ አደረጉት አስተዋጽ እናመሰግናለን። የእነርሱ ሃሳቦች፣ አስተያየቶች፣ እና ምክሮቻቸው እጅግ ጠቃሚ ናቸው።


MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ROCKVILLE, MARYLAND

# ሰክሽን 504 ለመተግበር የአፈጻጸም መመሪያ መጽሔት

**የተልእኮ መግለጫ**

**የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (DSES) ተልእኮ ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ 21 ዓመት የዕድሜ ክልል ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች ለሥራ፣ለኮሌጅ፣ እና ለማህበረሰብ የማዘጋጀት ትምህርት መስጠት፣ መተግበር፣እና አገልግሎት ሳይቋረጥ መሰጠቱን መቆጣጠር ነው**

## *መግቢያ*

ስንክልና ያለባቸውና መመዘኛዎችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች እኩል እድል የመስጠት ዓላማ የሰክሽን 504 የተሃድሶ ደንብ 1973 እና የአካል ስንክልና ያለባቸው አሜሪካውያን የማሻሻያ ደንብ 2008 /Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973 and the Americans with Disabilities Act Amendments Act of 2008 ዓላማ ነው። ይህ ግብ በተግባር የሚተረጎመው፣ የመጠቀም መብት፣ ጥቅማጥቅሞችን ማግኘት፣ አገልግሎቶች፣ እና ስንክልና ላለባቸው እና ስንክልና ለሌለባቸው ሰዎች እኩል ተፈጻሚነት ያለው እርዳታ/ድጋፍ፣ እና በአካል ስንክልና ምክንያት ከአድሎአዊነት የፀዱ ፕሮግራሞችን እና እንቅስቃሴዎችን/ሥራ ስለ መስጠት ይሆናል።

እኩልነት ማለት/አያያዝ ብቻ ሳይሆን እኩል እድል መስጠትም አድሎአዊነትን ለማስወገድ አስፈላጊ ነው። ተመሣሣይ አያያዝ የሚባለው መርህ ብቻውን አንዳንድ ጊዜ ስንክልና ያለባቸው ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን የተመቻቹ የሥራ እድሎች፣ ለትምህርት፣ ወይም አገልግሎቶችን ለማግኘት አያስችላቸውም።

የተረጋገጠ ስንክልና ያለባቸው ሰዎች ልዩነት/አድልዎ ሊደረግባቸው እንደማይገባ የፌደራል ህጎች ይደነግጋሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ከፌዴራል የገንዘብ ድጎማ/ ፈንድ የሚያገኝ ስለሆነ፣ የትምህርት ሥርአቱ የተሃድሶ ደንብ 1973/Rehabilitation Act of 1973 የማስፈጸም ሃላፊነት ይኖርበታል። በተለይም፣ MCPS በተለምዶ ሰክሽን 504 ተብሎ የሚታወቀውን የዚህን ድንጋጌ ክፍል የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት፡-

> በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አካለ ስንኩል የሆነ ሰው ማንኛውም ተገቢነት ያለው/ያላት ግለሰብ በአካል ስንክልና ምክንያት ከመሳተፍ፣ ከጥቅማጥቅሞች፣ ወይም ከማናቸውም ከፌደራል ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች/ሥራዎች ወይም የፌደራል ፋይናንስ እርዳታ/ ድጋፍ ከማግኘት የመከልከል/የመታገድ/የመካድ አድልዎ ሊደረግበት/ሊደረግባት አይችልም።

*ይህ መምሪያ መጽሀፍ ስለ ተማሪዎች በሰክሽን 504 መሠረት ከለላ ለማግኘት እና/ወይም ለመረዳት የሚገባውን ሒደትና መመዘኛዎችን ያብራራል። ስለ ሰክሽን 504 አፈጻጸም የት/ቤት ሥርአቱን ለመርዳት ደንቦቹ የተዘጋጁት በዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት አማካይነት ነው። እነዚህ ደንቦች ለዚህ የአፈጻጸም መምሪያ ህጋዊ መሠረት ይሰጡታል።*

*መምሪያ መጽሐፉ የተጻፈው የ MCPS ተልእኮን መሠረት ያደረገ "ማንኛዉም ተማሪ በአካደሚክ ትምህርት፣ ችግሮችን ለመፍታት የፈጠራ ችሎታ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ችሎታ ኖሮት/ኖሯት በኮሌጅ እና በሥራ ስኬታማ እንዲሆን/እንድትሆን ነው።"*

ከዚህ ተልዕኮ ጋር ተመሣሣይነት ያለው፣ በ 2017 የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የሚከተሉትን ለማከናወን ቁርጠኝነቱን የሚያረጋግጥ በ ፖሊሲ/Policy ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት/ፍትሃዊነት፣ እና የጎለበተ ባህል ላይ አጠቃላይ ማሻሻያ አድርጓል፡-

> *ሁሉንም ተማሪዎች ዓለም አቀፋዊ ማህበረሰብነት አመለካከት ይዘው እንዲኖሩና እንዲሠሩ የሚያዘጋጅ ማዕቀፍ በመዘርጋት ማበረታታት/ማነቃቃት ሁሉንም እንደየግል ልዩነቶቻቸው የሚያቅፍ መልካም የትምህርት አካባቢ መመስረትና ማስፋፋት።*

ስንክልና ያለባቸውና ለሰክሽን 504 ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በስንክልና ምክንያት ልዩነት እንዳይደረግባቸው ለመከላከል ከሌሎች ስንክልና ለሌለባቸው እኩዮቻቸው ከሚሰጠው የተለየ ድጋፎችና ወይም እርዳታዎች  ከፍተኛ-ደረጃ ስልጠና መጨመር ያስፈልግ ይሆናል።

የትምህርት ቤቶቻችን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወሰነው በደንብ የሰለጠኑ፣ ቁርጠኝነት ያላቸው፣ እና ደንታ በሚኖራቸው ሠራተኞች ላይ ነው። ለተለያዩ ዓይነት የተማሪ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት ሁሉም በማስተማር ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ሰፊ የተዋናይነት ሚና መጫወት እንዲችሉ የማስተማር ስልቶችን በአስፈላጊ መሣርያ ማደርጀትና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

## ለተማሪ የሰክሽን 504 ድጋፍ የማግኘት ብቃት መወሰን

### አጭር መግለጫ

ይህ ክፍል ስለ ተማሪው/ዋ በተሃድሶ ደንብ 1973 ሰክሽን 504 መሠረት ከለላ ለማግኘት እና/ወይም ለመረዳት የሚገባው/ብቃት ያለው ወይም ብቃት ያላት መሆን አለመሆኑን/ኗን ለመለየት ሒደት ለ MCPS የሥራ ባልደረቦች መመዘኛዎችን/መመሪያዎችን ያቀርባል። ሰክሽን 504 ግምገማ ለማካሄድ ተፈላጊና ህጋዊ ስለሆነ ብቁነትን ከመወሰን ጋር የተያያዙ ፍቺዎችና ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል።

### ወደ .. የማስተላለፍ ሂደት/Referral Process

ስንክልና እንደሚኖርበት/እንደሚኖርባት የሚጠረጠር/የምትጠረጠር ተማሪ ነገር ግን ገና ያልተለየ/ች ስንክልና ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ደንብ/Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) በት/ቤቱ እና/ወይም በተማሪ ወላጆች/ሞግዚቶች አማካይነት ለሰክሽን 504 ግምገማ ሊያስተላልፉት/ሊያስተላልፏት ይችላሉ።[1]የማስተላለፊያ ጥያቄው እንደደረሰ፣ የሰክሽን 504 ግምገማ ስብሰባ ቀጠሮ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶ ለወላጆች/ሞግዚቶች ይነገራቸዋል።

በዚህ ወቅት በሚስጥራዊነት የሚያዝ ፋይል ሊኖር ይገባል። ከሰክሽን 504 ጋር የሚገናኙ ሠነዶች በሙሉ በአውታረ-መረብ MCPS የተጠቀመባቸውን የ504 platform ጨምሮ በተማሪው/ዋ ሚስጥራዊ ፋይል ውስጥ ይቀመጣል።

### የሰክሽን 504 ውሳኔ ሰጪ ቡድን

የሰክሽን 504 ደንቦች የሚደነግጉት በሰክሽን 504 መሠረት የሚወሰኑ ውሳኔዎች መከናወን ያለባቸው፣ "ስለልጁ/ስለልጅቱ የሚያውቅ/የምታውቅ ሰው፣ የግምገማ መረጃዎቹን ትርጉም የሚያውቅ ሰው፣ እና ለምደባ ያለውን የተሻለ አማራጭ በሚያውቁ ሰዎች አማካይነት ነው"።

በ MCPS፣ የሰክሽን 504 ግምገማ የማካሄድ ሃላፊነት (እና ሌላም የሰክሽን 504 ውሳኔ የመስጠት) የተሰጠው በትምህርት ቤት ለተመሠረተ የሰክሽን 504 ቡድን ነው።

ለሰክሽን 504 ብቁነት ሲታሰብ፣ ርእሰ መምህራን ስለ ሰክሽን 504 ተፈላጊ ነገሮችን የሚያሟሉ ግለሰቦችን ሠራተኞች ቡድን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪው/ተማሪዋ የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት፣ ስንኩልነት ይኖርበ(ባ)ታል በሚል ጥርጣሬ ላይ ከሆነ የቡድን አባላት አመራረጡ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ፡- የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልና ከሆነ የተጠረጠረው፣ የት/ቤት ነርስ እና ባለሙያ ወይም የአካል ቴራፒስት የቡድን አባላት ቢሆኑ ይመረጣል። የአእምሮ ወይም ስሜት የመቆጣጠር ችግር (ትኩረት የማጣት ችግርን ጨምሮ) ግምገማ ለማድረግ ሲታሰብ የት/ቤት ሳይኮሎጂስት የቡድኑ አባል ቢሆን/ብትሆን ይመረጣል።

### ለሰክሽን 504 የግምገማ ስብሰባ ዝግጅት

የሰክሽን 504 ግምገማ ሲጠየቅ፣ ጥያቄ በቀረበ 30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ እንደሚደረግ የጊዜ ቀጠሮ ተይዞ ለወላጆች/ሞግዚቶች የስብሰባው ቀን እና ሠዓት ይገለጽላቸዋል። ከስብሰባው አስቀድሞ የተማሪው/ዋ ፋይሎች ለአባላቱ እንዲመለከቱት መሰጠት አለበት። ወላጆች/ሞግዚቶች ከ MCPS ውጪ በሆነ አካል ግምገማ የተደረገበት ሠነድ በMCPS ባለሙያ እንዲገመገም/እንዲታይ አቅርበው ከሆነ በተገቢ ባለሙያ መሞላት አለበት የ MCPS ቅጽ 336-68የቡድን ውጫዊ ሪፖርቶችን መመርመር/ማገናዘብ።

በስብሰባው ወቅት አዲስ የተሰጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን፡- ወላጅ / ሞግዚት በስብሰባው ወቅት በ MCPS ባለሞያ መደበኛ ግምገማ ማድረግ የማይቻል አዲስ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ካቀረበ/ች፣ መረጃውን ለመለዋወጥ በስብሰባው ላይ ፍቃደኛነት እንዲሰጥና እና ሌላ ስብሰባ በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲከናወን የጊዜ ቀጠሮ ይያዛል።

### የሰክሽን 504 የግምገማ ስብሰባ ማካሄድ

አንድን ተማሪ ስለ ሰክሽን 504 ግምገማ ሲደረግ፣ የሰክሽን 504 ቡድን ከተለያዩ ምንጮች (ተገቢ ከሆነ ከወላጆች/ከሞግዚት እና ከተማሪ ጭምር) መረጃዎችን መመልከት አለበት። የሰክሽን 504 ቡድን ስለ ተማሪው/ዋ ያለውን መረጃ ፈጥኖ የመረዳት አቅም/የተፈጥሮ ተሰጥኦ/አፕቲትዩድ፣እና የቴስት ውጤቶችን፣ የሪፖርት ካርዶችን፣ የመምህር ሪፖርቶች፣ የማስተዋል ሁኔታዎች፣ የትምህርት እና የጤና ሪኮርዶችን፣ የመላመድ/የመስማማት ባህርይ፣ እና ሜዲካል፣ ስነልቦናዊ፣ እና የአስተዳደግ/developmental ሪፖርቶችን ይገመግማል። ቡድኑ ለወላጅ/ሞግዚት ስለ ተማሪው/ዋ የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት ለመወያየት እና ለማስረዳት ስለ ሰክሽን 504 ብቁነት ክትትል እንደሚደረግም ለመግለጽ እድል መስጠት አለበት።

በሰክሽን 504 ለመታቀፍ ብቁ ለመሆን የሚከተሉት መረጃዎች መሟላት አለባቸው ይኼውም፡-

1. ተማሪው/ዋ የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት አለበት/አለባት[2]
2. የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት ዋና/ትልቅ የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ያደርጋል፣ እና
3. የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት ከፍተኛ የህይወት እንቅስቃሴን ይገድባል፣ ከፍተኛነቱም የሚለካው የተማሪውን/የተማሪዋን ዋና ክንውኖችን ስንክልና ከሌለባቸው እኩዮቻቸው ክንውን ጋር በማወዳደር/በማስተያየት ነው።

### ተማሪው/ዋ የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት እንዳለበት/እንዳለባት መወሰን

በሰክሽን 504 መፍቻ ላይ እንደተገለጸው "የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንኩልነት" ማለት "ማናቸውም የአካል መዛባት ሁኔታ (physiological disorder or condition)፣ የመልክ፣ የቅርፅ ወይም የገፅታ መበላሸት/መጥፋት (cosmetic disfigurement)፣ ወይም ከሚከተሉት የሰውነት ክፍሎች አንድ ወይም የበለጠ የአካል ጉዳት የደረሰበ(ባ)ት፡- የነርቭ (neurological)፣ ሥርአተ ጡንቻ መላላት (musculoskeletal)፣ ልዩ የስሜት ክፍሎች (special sense organs)፣ የመተንፈሻ አካል (respiratory) የመነጋገሪያ ክፍሎችን ጨምሮ (speech organs) የልብ (cardiovascular)፣ የመዋለጃ/የመራቢያ (reproductive)፣ ሥርአተ ልመት/ምግብን ማዋሃድ አለመቻል (digestive)፣ አባለ ዘር-ሽንት መሽኛ/መፀዳጃ (genito-urinary)፣ ደም እና በደም ስር ውስጥ ያለ ፈሳሽ ነገር (hemic and lymphatic)፣ የቆዳ እና የደምስር እጢዎች(endocrine)፣ ወይም የአእምሮ ወይም ስነልቦናዊ መዛባት እንደ አእምሮ ዘገምተኛነት (mental retardation)፣ የአእምሮ አካላዊ የበሽታ ምልክቶች (organic brain syndrome)፣ ስሜታዊነት ወይም የአእምሮ በሽታ (emotional or mental illness)፣ እና የተለየ የመማር ስንክልና።" 34 C.F.R. § 104.3.

---

[1]ተማሪው(ዋ) ለ IDEA ብቃት ካለው(ካላት) ተማሪው(ዋ) በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለማግኘት ብቃት ይኖረዋል/ይኖራታል፣ ነገር ግን IEP እና የሰክሽን 504 እቅድ ሁለቱን በአንድ ላይ አያ(ታ)ገኝም። ነገር ግን፣ IEP ማናቸውንም በሰክሽን 504 አስፈላጊ መጠቀሚያዎችን/accommodations ማሟላት ይኖርበታል፣ ለምሳሌ፡- የኦቲስቲክ ተማሪ የስኳር በሽታም ካለበት። በ ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት የዜጎች መብት ጽ/ቤት ስለ ሰክሽን 504 እና ስንክልና ስላለባቸው ተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች፣ ጥያቄ 36ን ይመልከቱ።

[2]እባክዎን ስለ "ስንክልና" መግለጫ እና የዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት ምሳሌዎችን ቃላትና ፍቺዎቻቸው/Glossary ላይ የተንፀባረቀውን የተሟላ ትርጉም ያገናዝቡበኤለመንተሪ እና ሁለተኛ ደረጃ የህዝብ ት/ቤቶች ስለ ሰክሽን 504 የወላጅ እና አስተማሪ መገልገያ/Resource መመሪያ

የተማሪው/ዋን ስንክልና በተመለከተ የሰክሽን 504 ቡድን ያሉትን ሠነዶች/ማስረጃዎች ይቀበላል/ያገናዝባል። ቡድኑ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልግ መሆኑን ካመነበት ቡድኑ ከወላጅ/ከሞግዚት የፈቃድ ማስረጃ በመጠየቅ ግምገማዎች እንዲካሄዱ መወሰን ይችላል። MCPS ቅጽ 336-31ግምገማ የማድረግ ፈቃድ። MCPS ቅጽ 270-2a፣ ለትምህርት ቤት የስነልቦና ባለሙያ/ሳይኮሎጅስት ስለ ሰክሽን 504 ትኩረት የማጣት ግምገማ/ምርመራ ፈቃድ መስጠት መሞላት ያለበት ቡድኑ ተማሪው/ዋ የማተኮር/የመከታተል ችግር ያለበት እና የውጪ ምርመራ ያልተደረገለት/ያልተደረገላት ከሆነ ነው። የውጭ ምርመራ ማካተት ያለበት መደበኛ የሆኑ ምርመራዎች፣ ከዶክተሮች ደብዳቤ፣ እና መድሃኒት/ፕሪስክሪፕሽን የታዘዘበት ማስታወሻ። ቡድኑ ከውጪ ምርመራ የተደረገበትን ተጨማሪ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን ለመሰብሰብ ከወላጅ/ሞግዚት ቅጽ ሞልተው ፈቃድ መቀበል አለበት MCPS ቅጽ 336-32፣ሚስጥራዊ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመስጠት/ለመለዋወጥ ፈቃድ መስጫ።

> በሰክሽን 504 መሠረት አንድ ተማሪ በሰክሽን 504 ለመታቀፍ አካላዊ ወይም የአእምሮ ዘገምተኛነቱ/ቷ በትምህርቱ/ቷ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊኖርበ(ባ)ት ያስፈልጋል የሚባል በህግ የተደነገገ ነገር እንደሌለ እባክዎ ይወቁ።

## በድክመት/በስንኩልነት ምክንያት የተስተጓጎሉ ዋና የህይወት/የኑሮ ሁኔታዎች መወሰን።

በሰክሽን 504 መሠረት "ዋና የህይወት/የኑሮ እንቅስቃሴዎች" ዝርዝር የሚያካትተው፣ (በዚህ አይወሰንም) ራስን መንከባከብ፣ በእጅ በአካል የሚሰሩ ሥራዎችን ማከናወን፣ መራመድ፣ ማየት፣ መስማት፣ መናገር፣ መተንፈስ፣ መማር፣ ሥራ መስራት፣ መቆም፣ ማንሳት/ከፍ አድርጎ፣ ማጎንበስ፣ ማንበብ፣ ማተኮር፣ ማሰብ፣ እና መገናኘት"። 34 C.F.R. § 104.3 and 29 C.F.R. §1630.2. ዋና የአካል ስራዎች-አገልግሎት በህጉ መሠረት ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎች ናቸው። እነዚህም ዋና የአካል ስራዎች የሚያካትቱት በትክክል የሚሠራ አንጀት(functions of the bowel)፣ የሽንት ፊኛ (bladder)፣ እና ጭንቅላት/አንጎል (brain)፣ ጤናማ የህዋስ እድገት (normal cell growth)፣ እና በሰውነት ውስጥ በሽታን የመከላከል ሥርአት (and the immune)፣ የተለያዩ እጢዎች endocrine (ለምሳሌ:- እድገትን የሚቆጣጠር እጢ/thyroid፣ በስረኛው የአንጎል ክፍል የሚገኝ የሰውነትን እድገት የሚቆጣጠር ሆርሞን አመንጪ እጢ/pituitary፣ እና ጣፊያ/pancreas)፣ መተንፈሻ (respiratory)፣ መራቢያ (reproductive)፣ የደም ዝውውር (circulatory)፣ የምግብ ውህደት (digestive)፣ እና የነርቭ ሥርዓቶች (neurological systems)።

> በተማሪው/ዋ ስንኩልነት ምክንያት ከአንድ በላይ ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ሊስተጓጎል ስለሚችል እባክዎን ማጤንና መመዝገብ ያስፈልጋል።

ቡድኑ በተማሪው/በተማሪዋ የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ያላቸውን ነገሮች የሚገልጹ ያሉትን መረጃዎች እና የሰክሽን 504 የብቁነት ማረጋገጫ ቅጽ በድረ-ገጽ ውጥን ላይ አጠናቆ ይሞላል።

## አካላዊ ወይም የአእምሮ ስንኩልነት በተማሪው/በተማሪዋ ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ስለማድረጉ/እንደሚገድብ መወሰን

በአካለስንኩልነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ ማሻሻያ 2008/The Americans with Disabilities Act Amendments Act of 2008 (ADAAA) በከፍተኛ ደረጃ የሚያስተጓጉሉ ነገሮችን በስፋት እንዲተረጎሙ/revisions require that the consideration of a substantial limitation be "broadly interpreted" ይጠይቃል። ሆኖም ግን ስለ ስንኩልነት መሠረታዊው ትርጉም አልተለወጠም። እነዚህ ክለሳ/ማሻሻያ የተደረገባቸው ADAAA ለሰክሽን 504 ጭምር ይሰራሉ። ያም ሆኖ ተማሪው/ዋ በዋና የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ከባድ ተጽእኖ የሚያስከትልበ(ባ)ት ስንክልና ሊኖርበ(ባ)ት ይገባል። የሆነ ሆኖ፣ ስንክልናው ተማሪውን/ተማሪዋን ከዋና የህይወት እንቅስቃሴው/ዋ ጭራሹኑ መከልከል ወይም በአሰቃቂ ሁኔታ ሊገድበው/ሊገድባት አይገባም።

የሴክሽን 504 ቡድን በጥያቄ ውስጥ የተካተተውን ዋና የሕይወት እንቅስቃሴ እና ምን አይነት ገደቦች በእንቅስቃሴው ላይ ተጽእኖ እንደሚሳድሩ የሚያሳይ የቀረቡ ሰነዶችን ያገናዝባል። ቡድኑ መገንዘብ ያለበት የተማሪው/ዋ ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን ማስተያየት/ማወዳደር ያለባቸው ስንክልና የሌለባቸው ተማሪዎች ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎች ጋር መሆኑን ነው።

ግለሰቡ/ግለሰቧ በከፍተኛ መጠን ከዋና የህይወት እንቅስቃሴ መገደቡን ለመወሰን፣ ስንክልና ከሌለባቸው የተማሪው/የተማሪዋ እኩዮች ጋር በማወዳደር መመልከቱ ይጠቅማል። ግለሰቡ/ግለሰቧ ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውንበት/የምታከናውንበት ሁኔታ፣ ዘዴ፣ ፀባይ፣ አይነት ወይም ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚፈጅበ(ባ)ትን ያክል ጊዜ ወይም ግለሰቡ/ቧ ለሚሠራው ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ሥራ የሚወስድበ(ባ)ት የጊዜ መጠን፤

ማረጋገጫዎችን ማገናዘብ፣ ለምሳሌ ሁኔታ፣ ዘዴ፣ ፀባይ፣ አይነት፣ ወይም የጊዜ መጠን (ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም)፣ አስቸጋሪነቱን መገንዘብ፣ ትጋት፣ ወይም ዋና የህይወት እንቅስቃሴን ለማከናወን የሚያስፈልገው የጊዜ መጠን፣ ዋና የህይወት እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት የሚሰማ ህመም፣ ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚያስፈልገው የጊዜ ርዝመት፣ ወይም መደረግ ያለበትን ዋና የአካል እንቅስቃሴ ስንክልናው የሚያደናቅፍበት ሁኔታ።

## ሁኔታውን የመቀነስ/የማቅለል እርምጃዎች የማሻሻል ውጤቶች

ስንክልናው ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጎዳ መወሰን ያለበት ሁኔታውን ለመቀነስ/ለማቅለል የማሻሻል እርምጃዎች በሚከተለው ዓይነት ከመታሰባቸው አስቀድሞ ነው።

1. መድሐኒት፣ የህክምና አቅርቦቶች፣ መሣሪያዎች፣ ወይም መገልገያ መሳሪያዎች፣ ዝቅተኛ/አነስተኛ - የማየት ችግር (መደበኛውን የዓይን መነጽር ወይም ኮንታክት ሌንስ አይጨምርም)፣ ሰው ሰራሽ የአካል ምትክ (prosthetics) (የአካል ቅጥያ ክንድ/እግር የመሳሰሉ መሣሪያዎች)፣ የማዳመጫ መሣሪያ እና በቀዶ ጥገና የተተካ አካል/hearing aids and cochlear implants ወይም ሌላ implantable hearing devices/በቀዶ ጥገና ለመተካት የሚያስችሉ የመስሚያ መሣሪያዎች ወይም ሌላ የመንቀሳቀሻ መሣሪያዎች፣ ወይም ኦክስጂን ህክምና መርጃ መሣርያ እና አቅርቦቶች። "ዝቅተኛ-የማየትን ችግር የሚረዳ መሣሪያ" ማለት አጉልቶ የሚያሳይ፣ ዝቅተኛ የማየት ችሎታን የሚያሻሽል፣ ካልሆነም የሚታየውን ምስል/ገፅታ ጥራት የሚጨምር ማለት ነው።
2. አጋዥ ቴክኖሎጂን መጠቀም፤
3. ተገቢ የሆነ/ደህና የሚረዳ መጠቀሚያ/accommodations ወይም መቀየሪያ መሣሪያዎች/auxiliary aids ወይም አገልግሎቶች፣
4. የተለመደ ባህሪይ ወይም ተስማሚ የነርቭ ህዋስ ማሻሻያዎች/ለዉጦች።

በተራ የዓይን መነፅር ወይም ኮንታክት ሌንስ ለማቅለል እርምጃ መወሰድ ያለበት ስንክልናው የህይወት እንቅስቃሴን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሰናክል መሆኑን ሲታወቅና የሚያስከትለው መሻሻል ሲረጋገጥ መሆን አለበት። "ተራ የዓይን መነፅር ወይም ኮንታክት ሌንስ" ማለት የማየትን ንቁነት/ችሎታ ሙሉ በሙሉ ያስተካክላል ተብሎ የታሰበ ወይም የጨረር/ማንፀባረቅ አቅጣጫን ችግርን እንዲያስወግድ የታለመ ነው።

የግለሰቡ(ቧ) ስንክልና ዋና የህይወት እንቅስቃሴን እንደሚገድብ ለመወሰን ሁኔታውን የማቅለል/የማሻሻል እርምጃዎች (የመድሃኒት ጎጂ ጎኖችን የመሳሰሉት ወይም ህክምናውን ከመከታተል ጋር በተያያዘ የሚያስከትለውን ጫና) በተጨማሪ ማገናዘብ ያስፈልጋል።

"የሰክሽን 504 ስብሰባ ላይ ግምገማ ሲደረግ" ተማሪው(ዋ) ሦስቱንም (ሁሉንም) አስፈላጊ ነገሮች ከማሻሻያ እርምጃዎች ዉጪ፣ የሚያሟላ/የምታሟላ ከሆነ ተማሪው(ዋ) ለሰክሽን 504 እቅድ ብቁ ይሆናል/ብቁ ትሆናለች።

### ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው ነገሮች

1. ትኩረት ማጣት፣ ቅብጥብጥነት የጤና ችግር፣ መዝረክረክ/ADHD፡- የተማሪው(ዋ)ን በትኩረት የመከታተል ችግር፣ ቅብጥብጥነት/ADHD እንዳለበ(ባ)ት ለመገምገም የት/ቤት ሳይኮሎጂስት የቡድኑ አባል መሆን አለበ/ባት። የት/ቤት ሳይኮሎጂስት ቅጹን በመሙላት ቡድኑን መርዳት ይኖርበ(ባ)ታል MCPS ቅጽ 270-2A, ሰክሽን 504 ትኩረት ያለማድረግ ችግርን/መዛባትን ለመገምገም ለት/ቤት ሳይኮሎጂስት የሚሰጥ ፈቃድ፣ ወላጅ/ሞግዚት ከውጭ ምርመራ/ግምገማ የተደረገት ማስረጃ አቅርበው ካልሆነ በስተቀር። ቡድኑ በቀጣዮ የሰክሽን 504 ስብሰባ ወቅት ለመገምገም ተጨማሪ መረጃ/ዳታ ማግኘት ይኖርበታል። ለተጨማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን እባክዎ የጁላይ 26/2016 መልክት ይመልከቱ፡- ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ የዜጎች መብት ጽ/ቤት፣ ለ ባልደረባ ደብዳቤ እና ለ ADHD ተማሪዎች የመፍትሔ መገልገያዎች/ቋት መመሪያ (U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Dear Colleague Letter and Resource Guide on Students with ADHD)።
2. ጊዜያዊ እና ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር የተገናኘ ተደጋጋሚ ስንክልና፡- በሰክሽን 504 መሠረት፣ ትክክለኛው የብቁነት ግምገማ ስንክልናው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ በመሆኑ አይደለም። የጊዜያዊ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ስንክልና፣ አካል ጉዳተኝነቱ ወሳኝ መሆኑን በተመለከተ ምላሽ ለመስጠት እንደየ ጉዳዩ በመመስረት፣ ስንክልናው የቆየበትን ያክል ጊዜ (ይቆያል ተብሎ የሚታሰበውን ጊዜ) እና የተገደበውን ዋና የተማሪው(ዋ)ን እንቅስቃሴዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ነዉ። በየምክንያቱ ወቅት ጠብቆ የሚነሳ ስንክልና ወይም ውስጥ የተደበቀ ስንክልና በሚነሳበት ጊዜ ዋና የህይወት እንቅስቃሴን የሚገድብ ከሆነ በሰክሽን 504 መሠረት ብቁ ለመሆን ያስችላል።
3. ከፍተኛ ችሎታ/ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች፡- ተማሪው/ዋ ከፍተኛ ችሎታ/ተሰጥኦ ስላለው/ስላላት እና በላቀ ደረጃ ስለተመደበ(ች)፣ የክብር ደረጃ፣ ማግኔት ፕሮግራሞች፣ ወይም ዓለም አቀፋዊ የ Baccalaureate ዲፕሎማ ፕሮግራም ክፍሎች ላይ መመደብ በቀጥታ ከሰክሽን 504 ብቁነትን አይከለክልም/አያግድም። ከፍተኛ ችሎታ/ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ አካላዊ ወይም የአእምሮ ስንክልና ሊኖርባቸው ይችላል። ለእንደዚህ ዓይነት ተማሪዎች የሚሰጥ ማናቸውም ዓይነት መገልገያዎች/accommodations ተማሪውን/ተማሪዋን ለላቀ ደረጃ ወይም ለክብር ተማሪነት እንዲያስመድብ ሳይሆን "ሁኔታውን ደልዳላ አድርጎ የሚያስተካክል" መሆን አለበት። ከፍተኛ ችሎታ/ተሰጥኦ ያለው/ያላት ተማሪ መገልገያ/መጠቀሚያ ነገሮችን/ accommodations በቀጥታ መከልከል የለባቸውም። ተማሪው/ዋ ባለበ(ባ)ት ስንክልና ምክንያት ማናቸውንም በ MCPS የሚሰጡ ወይም MCPS ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ፕሮግራሞች ላይ ወይም እንቅስቃሴዎች መዳረሻን የሚገድብ ከሆነ ብቁ ይሆናል/ትሆናለች።
4. በግል ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች፡- ወላጆች/ሞግዚቶች ጥያቄ ካቀረቡ የ MCPS ሰክሽን 504 ቡድኖች በግል ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን መገምገም ይኖርባቸዋል። የሰክሽን 504 ቡድን ስለ ሰክሽን 504 ግምገማ ያጠናቅቃል ነገር ግን ብቁ የመሆን ውጤቱ ምንም ይሁን የሰክሽን 504ን እቅድ አይሠራም። ተማሪው/ዋ ወደ MCPS ከገባ/ች፣ ለተማሪው ተስማሚ ቦታዎች/accommodations ባሉበት የሰክሽን 504 እቅድ ይዘጋጃል። ወላጆች/ሞግዚቶች የግምገማ መረጃዎቻቸውን ወደ ግል ት/ቤታቸው ለመውሰድ ይችላሉ።
5. የጤንነት ሁኔታዎች፡- በሰክሽን 504 መሠረት፣ የህመሙ ክብደት ሁኔታ እየታየ የጤና ስንክልና (ለምሳሌ፡- ለህይወት አስጊ የሆነ አለርጂ፣ የአስም በሽታ፣ እና የስኳር በሽታ) እንደ ስንክልና ሊቆጠሩ ይችላሉ። አብዛኛዎቹ የጤና ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በየግላቸው የጤና እንክብካቤ እቅድ ቢኖራቸውም (IHCP)፣ የሰክሽን 504 እቅድ ከ IHCP የሚለየው በመማሪያ ክፍል ውስጥ መለወጥ ያለባቸውን ነገሮች መመሪያ ይሰጣል እና በሌሎችም ቦታዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ጤናማ የትምህርት ግብ እንዲደርስ/እንድትደርስ እና በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎ እንዳይደረግበት/እንዳይፈጸምባት ይከላከላል። የ MCPS ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች/የአፈጻጸም ሂደቶች የተማሪው(ዋ)ን በተለይ የተጓደሉ ነገሮችን ለማሟላት በማይችሉበት ሁኔታ በት/ቤት እቅድ በት/ቤት፣ በተማሪው(ዋ)፣ እና በተማሪው(ዋ) ቤተሰብ መካከል የሰክሽን 504 እቅድ እንደ ተጨማሪ እርምጃ ይሆናል። በስኳር በሽታ ስለሚጠቁ ተማሪዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሚከተለውን ሠነድ ያገናዝቡ የሚሪላንድ ስቴት በት/ቤት የጤና አገልግሎቶች መመሪያ፣ በት/ቤቶች ስለ ስኳር በሽታ አያያዝ/ማኔጅመንት፣ ሜይ 2017 በሥራ ላይ የዋለ፡-

### ተማሪው/ዋ መገልገያዎች/መጠቀሚያዎች/accommodations ያስፈልገው/ያስፈልጋት እንደሆነ ስለ መወሰን

በሰክሽን 504 መሠረት ብቁ የሆነ የአካል ወይም የአእምሮ ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ በሙሉ የነፃ እና የተመቻቸ ህዝባዊ ትምህርት (FAPE) accommodations ተጠቃሚ ይሆናል/ትሆናለች ማለት አይደለም። ሆኖም፣ accommodations አስፈላጊ ባይሆኑ እንኳ፣ በሰክሽን 504 መሠረት በተማሪው(ዋ) ላይ በአካል ስንክልና ምክንያት አድሎ መደረግ ስለሌለበት ቡድኑ የሰክሽን 504 የብቃት መመዘኛ ቅጽ በድረገጽ ላይ እንደሁኔታው ቡድኑ ለመቀበል የወሰነበትን ምክንያትና መረጃዎችን ጠቅሶ መሞላት አለበት።

ተማሪው(ዋ) የሰክሽን 504 መመዘኛዎች የማያ(ታ)ሟላ ከሆነ(ች) የሰክሽን 504 ቡድን የተማሪው(ዋ)ን የተለየ/የሚታወቅ ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ተገቢ አስተያየት በ 504 ብቃት መመዘኛ ድረገጽ ላይ ይመዘገባል። በዚህ ሁኔታ ላይ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች የMCPS በራሪ ፅሁፍ ቅጂ/brochure፣በሂደት ላይ ስለ መረጃ አያያዝ ጥንቃቄ ኮፒ ሊሰጣቸው ይገባል። ሰክሽን 504 የ1973 የተሐድሶ ደንብ .

## ሰክሽን 504 የማሟላት ብቃት ላላቸው ተማሪዎች እቅድ ማዘጋጀት

### አጭር መግለጫ

የሰክሽን 504 እቅድ ለማዘጋጀት ይኼኛው ክፍል መመሪያ ይሰጣል። አንድ ተማሪ በሰክሽን 504 መሠረት ብቃት እንዳለው/እንዳላት ሲረጋገጥ የሰክሽን 504 ቡድን ተማሪው/ዋ በሰክሽን 504 መሠረት የሚያስፈልገውን/የሚያስፈልጋትን ነፃና ተገቢ የህዝባዊ ት/ምህርት (FAPE) መገልገያዎችን/accommodations አስፈላጊ ከሆነ እንዲያገኝ/እንድታገኝ እና የሰክሽን 504 እቅድም እንዲዘጋጅ ያደርጋል። በዚህ በህጋዊነት የሚዘጋጅ እቅድ ላይ ተማሪው/ዋ ባለበት የስንክልና ልዩ ሁኔታ አስፈላጊ ነገሮችን/accommodations ዝርዝር ይገለጻል። እቅዱ MCPS ለተማሪው መስጠት ያለበትን አስፈላጊ ነገሮች/accommodations እና አገለግሎቶች የሚገልጽ መግለጫ ነው።

## የሰክሽን 504 ቡድን

ርእሰመምህር የሰክሽን 504 መመዘኛዎች በሚያሟሉ ግለሰቦች የት/ቤቱን የሰክሽን 504 ቡድን የማቋቋም ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። በሰክሽን 504 መሠረት ውሳኔ መሰጠት ያለበት ስለ ልጁ/ልጅቱ እውቀት ያላቸውና የግምገማ መረጃዎቹን ትርጉም የሚያውቁ ሰዎች እንዲሁም የምደባ አማራጮችን ለመጠቀም በሚችሉ ሰዎች(ቡድን) አማካይነት እንዲሆን ያስፈልጋል። የሰክሽን 504 ቡድን ማካተት ያለበት፦

- ርእሰመምህር ወይም ተወካይ፣
- ከተማሪው ጋር እየሰራ ያለ ወይም ወደፊት የሚሠራ ቢያንስ አንድ መምህር(ት)
- ተገቢነት ያላቸው ተጨማሪ የሥራ ባልደረቦች፣ እንደ ት/ቤት የስነልቦና ባለሙያ/ሳይኮሎጂስት፣ የት/ቤት ካውንስለር፣ የተማሪዎች ጉዳይ ሠራተኛ (PPW)፣ የት/ቤት ነርስ፣ እና ማናቸውም ሌሎች እቅዱን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች። ለምሳሌ፦ የተማሪው/ዋ ችግር/ስንክልና አስም ከሆነ፣ የት/ቤት ነርስ የቡድኑ አባል መሆን አስፈላጊ ነው።
- ወላጅ/ሞግዚት የሰክሽን 504 እቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ እንዲሳተፉ መጋበዝ አለባቸው፤ እና
- አግባብነት ካለው ተማሪው/ዋ።

## ሰክሽን 504 እቅድ የማውጣት ዝግጅት

እቅዱን ለማውጣት ዝግጅት ሲደረግ፣ ቡድኑ የተማሪው(ዋ)ን የሰክሽን 504 የግምገማ ዝርዝር እና በዚህ ሳይወሰን፣ ሌሎች ወቅታዊ መረጃዎችን መመርመር ይኖርበታል —

- የሪፖርት ካርድ መረጃ፣
- የመምህር ሪፖርቶች፣
- በት/ቤት-የተከናወኑ ፈተናዎች/ቴስቶች፣
- በሥርዓተ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ግምገማዎችን፣
- መደበኛ ግምገማዎችን፤
- ወቅታዊ የጤና ምርመራ መረጃዎች እና/ወይም ወቅታዊ የህክምና ሁኔታዎች፣
- ለአካደሚክ እና/ወይም ለስነምግባር ጣልቃ-ገብ ሁኔታዎች ያለውን ምላሽ ሠነዶችን
- በክፍል-ደረጃ የቡድን ስብሰባዎች እና የምክር አገልግሎቶችን፣
- በቃል እና በጽሑፍ የቀረቡ የምልከታ-ማስተዋል ሠነዶችን፣
- የወላጆች አስተዋጽኦMCPS ቅጽ 336-39የወላጅ ሪፖርትአስፈላጊ ከሆነ ለመጠቀም ይቻላል፣ እና
- አግባብነት ካለው የተማሪው(ዋ) አስተዋጽኦ።

## የሰክሽን 504 እቅድ መጻፍ

የሰክሽን 504 ቡድን እቅድ/ፕላን ለማዘጋጀት በቂ መረጃ መኖሩን ካረጋገጠ፣ የሰክሽን 504 መመዘኛዎችን እንደሚያሟላ/እንደምታሟላ ከወሰነ በኋላ የእቅድ ዝግጅት መቀጠል ይችላል። ተማሪው(ዋ) የሰክሽን 504 ብቃት እንዳለው/እንዳላት ከተረጋገጠ በኋላ የሰክሽን 504 ቡድን ሌሎች ተጨማሪ ግምገማዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ካልወሰነ በስተቀር እቅድ መዘጋጀት ያለበት ከ30 ቀኖች ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው። ተማሪው/ዋ ለሰክሽን 504 ብቃት እንዳለው/እንዳላት ከተረጋገጠ በኋላ ተጨማሪ ግምገማ ማድረግ ካስፈለገ በ60 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት።

ከሴፕቴምበር 5/2017 ጀምሮ ቡድኑ ስለ ሰክሽን 504 እቅድ በድረገጽ ላይ መሙላት ይኖርበታል። በዚህ ቅጽ ላይ የእያንዳንዱ ተሳታፊ የቡድን አባል ስም እና የሥራ ድርሻ/ኃላፊነት መዘርዘር ይኖርበታል። ማናቸውም ተጨማሪ በስብሰባ ላይ የተመዘገቡ ማስታወሻዎች በሰክሽን 504 እቅድ ላይ በሚመለከተው ቦታ መገለጽ አለበት።

## የመነሻ/መሰረት መረጃ

ተማሪው/ዋ ለሰክሽን 504 ብቁ እንደሚሆን/እንደምትሆን ቡድኑ የወሰነበት ቀን በእያንዳንዱ እቅድ ላይ መገለጽ ይኖርበታል። እቅዱ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፦

- ስለ ብቃት ለመገምገም በተደረገ ስብሰባ ወቅት የተረጋገጠ የተለየ ስንክልና።
- በስንክልና ምክንያት የተደናቀፈ ከፍተኛ የህይወት እንቅስቃሴ።
- በገምጋሚው ቡድን አማካይነት ተለይቶ የታወቀ የትምህርት አስፈላጊ ነገሮች።

## የሴክሽን 504 ፕላን Section 504 Plan

እቅዱ መገልገያ ነገሮችን/accommodations፣ የፕሮግራም ማሻሻያዎችን፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን/instructional approaches፣ ተጨማሪ የመርጃ አገልግሎት አጠቃቀምን፣ እና ተማሪው(ዋ) ከፕሮግራሞች እና ከእንቅስቃሴዎች ስንክልና ከሌለባቸው ተማሪዎች እኩል ተጠቃሚ ለመሆን እድል ለመስጠት እንዲያስችል ትራንስፖርቴሽን/መጓጓዣ ማካተት አለበት። ማናቸውም እንዲተገበሩ አስተያየት የሚሰጥባቸው የመገልገያ ትግበራዎች/accommodations የሚከተለውን ማድረግ አለባቸው፦

- ድክመት/ስንክልና ካለበት ሁኔታ ጋር መገናኘት አለበት።
- ለተማሪው(ዋ) በተለይ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማንፀባረቅ አለበት።
- ተማሪው(ዋ) ስንክልና ከሌለባቸው ሌሎች እኩዮቻቸው ተማሪዎች ጋር እኩል ለመማር (ወይም ካልሆነም፣ እንደ ስንክልናው ሁኔታ ለመሥራት) የሚያስችል እድል የሚሰጥ፣
- ለተማሪው(ዋ) አግባብነት ያለው ወደ ስኬታማነትን የሚያመራ እኩል የትምህርት እድል  የሚሰጥ መሆን አለበት።
- መቼ እና እንዴት እቅዱ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው በግልጽ የሚያመለክት እንዲሆን (ቦታ) እና ለተግባራዊነቱ ኃላፊነት የሚመለከታቸውን ሰዎች የሚገልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል።

መገልገያዎቹ/Accommodations ከተማሪው(ዋ) ስንክልና ሁኔታ ጋር በቀጥታ የተገናኙ/የሚረዱ መሆን አለባቸው። ከስንክልናው/ዋ ጋር የማይገናኙ ተጨማሪ መገልገያዎች በሰክሽን 504 እቅድ ላይ መካተት የለባቸውም ነገር ግን በመምህሩ/ሯ የትግበራ ወቅት ሊቀርቡ ይችላሉ።

የሰክሽን 504 እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት የሰክሽን 504 ቡድን ማቅረብ ያለበት ለተማሪው(ዋ) ባለበት/ባለባት የአእምሮ ወይም የአካል ስንክልና ምክንያት ዋነኛ የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ  ባሳደረው ተፅእኖ ምክንያት አስፈላጊ የሆኑና በማስረጃ የተደገፉ መገልገያዎችን/accommodations ነው።

እንዲሁም፣ የሰክሽን 504 ቡድን መለየት ያለበት ለመደበኛ ትምህርት ፈተና/ቴስት አስፈላጊ ነገሮችን/accommodations እና በካውንቲ ወይም በስቴት ፈተና/ምዘና ወቅቶችም መስጠት ያስፈልግ እንደሆን መታወቅ ይኖርበታል። መገልገያዎቹ/Accommodations ከተማሪው(ዋ) የአእምሮ ወይም የአካል ስንክልና ሁኔታ ጋር በቀጥታ የተገናኙ/የሚረዱ መሆን አለባቸው።

### የስብሰባው ማጠቃለያ

የሰክሽን 504 ቡድን የሚከተሉትን በማከናወን ስብሰባውን ያጠቃልላል፦

- በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ዳግመኛ ግምገማ የሚያደርግበትን ቀን ይወስናል።
- ጉዳዩን በተለይ የሚከታተል ሰው/case manager (ለምሳሌ፦ የክፍል መምህር/ት፣ የት/ቤት ካውንስለር፣ የቡድን መሪ) ይለያል፣
- ከወላጅ/ሞግዚት ስብሰባ ላይ መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ ፊርማ ማግኘት።
- ሰክሽን 504 መጨረሻው ላይ የሚገኝ በሥራ ሂደት ላይ የሚገኝ የመረጃ አያያዝ ጥንቃቄ ለወላጆች/ለሞግዚቶች መስጠት።

ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተል/የምትከታተለው ሰው/case manager ከስብሰባ በኋላ እያንዳንዱን መከናወን ያለበትን መገልገያ/accommodations የማስፈጸም ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች የእቅዱን ቅጂ/ኮፒ የማሰራጨት ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተለው ሰው መሙላት ያለበ(ባ)ት MCPS ቅጽ 270-2d ሰክሽን 504 እቅድ ማሰራጨት ኃላፊነት የሚመለከታቸው ሰዎች በሙሉ የሰክሽን 504 እቅድ ቅጂ/ኮፒ ስለማግኘታቸው ለመግለጽ። እባክዎ ያስተዉሉ፡- ይኼ የሚያካትተው የት/ቤት ነርሶችን እና እንደ አግባቡ ለሥራው ቅርበት ያላቸውን አገልግሎት ሰጪዎችን ጭምር ነው።

## የሰክሽን 504 እርምጃ ማሻሻያ እና ዳግመኛ ግምገማ

### አጭር መግለጫ

የሰክሽን 504 ቡድን ስለ እያንዳንዱ በሰክሽን 504 መመዘኛ አሟልተው/ብቁ ሆነው የታቀፉ ተማሪዎችን የሚሰጣቸው አገልግሎት ተገቢ መሆኑን፣ አስፈላጊ መገልገያ ነገሮችን/accommodations፣ እና ወቅታዊ ማሻሻያ የተደረጉ ነገሮች ካሉ ዓመታዊ ዳግመኛ ግምገማ ማካሄድ አለበት። እንደአስፈላጊነቱ የግምገማ ስብሰባዎች ከዓመታዊ ቀን ቀጠሮ በፊትም ለማድረግ ይቻላል። የምደባ ለውጥ በሚደረግ ጊዜ ሁሉ ዳግመኛ ግምገማ መደረግ ይኖርበታል፣ ይህም ማለት ከ10 ቀናት በላይ እገዳ፣ በእገዳ የማግለል ቅጦች/pattern of removals for suspension፣ ማስወጣት፣ ወይም ማዛወር። በተጨማሪም፣ ወላጆች/ሞግዚቶች በማናቸውም ጊዜ የሰክሽን 504 እንደገና ግምገማ እንዲደረግ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ዓመታዊ የሰክሽን 504 እቅድ ዳግም ግምገማ ዓላማው ተማሪው(ዋ) በሰክሽን 504 አገልግሎቶች እና መገልገያ ነገሮች/accommodations መቀጠል እንደሚገባው(ት) ወይም እንደማይገባው(ት) ለማወቅ እና በወቅቱ እየተሰጡ ያሉት አገልግሎቶችና መገልገያዎች/accommodations ቢቀጥሉ አግባብነት ይኖራቸው እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል። በሰክሽን 504 እቅድ የታቀፉ ተማሪዎችን መገልገያዎች/accommodations የሚተገብሩ መምህራን በሙሉ MCPS ቅጽ 270-2c፣ የሰክሽን 504 ሂደት/እርምጃ እና የመገልገያዎች/Accommodation ግምገማ ወረቀት እና MCPS ቅጽ 272-7 የኤለመንተሪ መምህር ሪፖርት ወይም MCPS ቅጽ 272-8 የሁለተኛ ደረጃ መምህር ሪፖርት እና ለሰክሽን 504 ጉዳዩን በቅርብ ለሚ(ምት)ከታተል/case manager ቀጠሮ ከተያዘለት የስብሰባ ጊዜ አስቀድመው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

### የሰክሽን 504 እርምጃ/ለውጥ ዳግመኛ ግምገማ ስብሰባ።

የክለሳ ቅጹ በሚሞላበት ወቅት የሚከተሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው፦-

### የሰክሽን 504 እርምጃ ዳግመኛ ግምገማ

- ተማሪው(ዋ) አሁንም የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልና አለበ(ባ)ት?
- የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልናው እስካሁንም ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል?
- የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልናው ወደፊትም ዋና የህይወት እንቅስቃሴ መግታት ሊቀጥል ይችላል? (ስንክልናው በዋና የህይወት እንቅስቃሴ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ የሚወሰነው ስንክልና ከሌለባቸው እኩዮቻቸው እንቅስቃሴዎች ጋር በማወዳደር ይሆናል።)
- ተማሪው(ዋ) መገልገያ ነገሮችን/accommodations መፈለጉ(ጓ) ይቀጥላል?
- ተማሪው(ዋ) በወቅቱ በሰክሽን 504 እቅድ ላይ የተዘረዘሩትን መገልገያ ነገሮች/accommodations እየተጠቀመ/ች ነው? ካልሆነም፣ የትኞቹን መገልገያ ነገሮች/accommodations በተለይ የማይ(ት)ጠቀምባቸው እና ለምን?
- የሰክሽን 504 እቅድ መቀጠል አግባብ ይሆናል? ካልሆነም፣ መጨመር ወይም መወገድ ያለባቸው መገልገያ ነገሮች/accommodations ይኖራሉ?

### ተማሪው(ዋ) ምንም መገልገያ ነገሮችን/accommodations የማይፈልግ/የማትፈልግ ከሆነስ ምን ይሆናል?

የሰክሽን 504 ቡድን አባላት ተማሪው(ዋ) ብቁ እንደማይ(ት)ሆን ወይም ከሰክሽን 504 እንዲወገድ/እንድትወገድ ከመወሰናቸው አስቀድሞ ዳግም ግምገማ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ዳግመኛ ግምገማ ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ የተማሪው(ዋ)ን የሚያስፈልገውን/የሚያስፈልጋትን ወቅታዊ ሁኔታና በመደበኛነት መገልገያ ነገሮችን/accommodations ያስፈልግ/አያስፈልግ እንደሆነ መገምገም ነው። ወቅታዊውን የተማሪን ፍላጎት ዳግም ግምገማ ሲደረግ የሰክሽን 504 ቡድን ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን መገምገም ያስፈልጋል። ከሰክሽን 504 ለማስወገድ የሚደረጉ ውሳኔዎች በጠቅላላ ባሉት የጽሁፍ መረጃዎች መሠረት እየተገመገመ መሆን አለበት። ከዚህ በታች የተገለጹትን ብቁ የመሆን መመዘኛዎች በማመሳከር የሰክሽን 504 ቡድን ተማሪን ከሰክሽን 504 እቅድ የሚያስወግድበትን ምክንያት በአጭሩ መግለጽ አለበት።

### ብቁ የመሆን መመዘኛዎች

የሰክሽን 504 ቡድን በወቅታዊው መረጃ/ኢንፎርሜሽን ተሞርኩዞ የሚከተለው መስፈርት አሁንም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል እንደሆን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፦

1. ተማሪው(ዋ) የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልና አለበት/አለባት።
2. የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልናው ከባድ የህይወት እንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ያደርጋል።
3. የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልናው በከፍተኛ ሁኔታ የህይወት እንቅስቃሴን ይገድባል። በከፍተኛ መጠን የመገደቡ ሁኔታ የሚወሰነው በዋና የህይወት እንቅስቃሴ ላይ የተማሪውን አፈጻጸም፣ ብቃት፣ ቅልጥፍና ስንክልና ከሌለባቸው ጓደኞች/እኩዮች ጋር በማወዳደር ይሆናል።

ቡድኑ በተጨማሪም በሰክሽን 504 እቅድ የታቀፈ ተማሪ የ MCPS የትምህርት ፕሮግራም እና እንቅስቃሴዎችን መደበኛ መገልገያዎች/accommodations ሳይኖሩ(ሯ)ት ስንክልና ከሌለባቸው እኩዮች ጋር እኩል ለመስራት ይችል/ትችል እንደሆነ ማገናዘብ አለበት።

የሰክሽን 504 ቡድን አባላት የተማሪው ስንክልና "ከፍተኛ መሰናክል " እንደማይሆንበ(ባ)ት ከተማመኑ እና ተማሪው(ዋ) ለሰክሽን 504 ብቁ እንደማይሆን ካረጋገጡ ይህንኑ በግምገማ ቅጹ ላይ መግለጽ አለባቸው። ጠቅላላ ሠነዶቹ በተማሪው(ዋ) ፋይል በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው።

## ለሰክሽን 504 ተማሪዎች የዲሲፕሊን ሥርዓት

### አጭር መግለጫ

ምንም እንኳ በሰክሽን 504 ላይ ስለ ተማሪ ስነምግባር በስፋት የተገለጸ ደንብ ባይኖርም፣ በሰክሽን 504 እቅድ ውስጥ የታቀፊ/ች ተማሪ በዲስፕሊን ምክንያት ሲታገድም ሆነ ሲባረር የተሰወነ በግልጽ የተቀመጠ ከለላ አለ።

### በምክንያት የሚደረግ ስብሰባ ሒደት-ሥርዓቶች

በሰክሽን 504 ከለላ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እና የሰክሽን 504 እቅድ ከአንድ ዋነኛ ልዩ ሁኔታ በስተቀር/with one major exception እንደ ሌሎቹ አጠቃላይ ተማሪዎች አንድ ዓይነት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል። የሰክሽን 504 ተማሪ እንዲታገድ/እንድትታገድ እና ሌላ ከበድ ያለ የምደባ ለውጥ የሚያከትል አስተያየት ቀርቦ ከሆነ፣ አንዳንድ የአፈጻጸም ሒደት ሥርዓቶች ይኖራሉ። ከባድ የምደበ ለውጥ የሚገለጸው ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርት ገበታ ማስወጣት/መታገድ ነው። ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በተከታታይ ለ10 ቀናት ከክፍል መታገድ ወደ ማስወጣት/መባረር የሚያመራ ከሆነ "በክፍል ምደባ ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያስከትል" ሊሆን ይችላል።

በትምህርት ዓመቱ ከመባረሩ(ሯ) ከ10ኛው ቀን በፊት (ተከታታይም ሆነ የተጠራቀመ)፣ የሰከሽን 504 ቡድን ተሰብስቦ ተማሪው/ዋ የተባረረ(ች)በት መጥፎ ስነ ምግባር "የተፈጠረበት ምክንያት" ለሰክሽን 504 ብቁ ያደረገዉ/ጋት ስንክልና መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

በተፈጠረው ምክንያት የሚደረግ ስብሰባ እንደተለመደው የሚያካትተው እነዚያኑ የተማሪው(ዋ)ን ዓመታዊ ግምገማ ለማድረግ የተሳተፉ የሰክሽን 504 ቡድን አባላት ናቸው። ስለ ግምገማ መረጃዎቹ እና የምደባ አማራጮችን ማወቅ በተጨማሪ፣ የሰክሽን 504 ቡድን አባላት ስለተማሪዎቹ እና ስላለባቸው ስንክልና ማወቅ አለባቸው።

በተፈጠረው ምክንያት የሚደረግ ስብሰባ በዲስፕሊን ምክንያት ከክፍል የማገድ/የማስወገድ አጀማመር እንደተከሰተ በተቻለ ፍጥነት የስብሰባ ጊዜ ቀጠሮ ተይዞ ለወላጅ/ሞግዚትም ስብሰባው የሚደረግበትን ምክንያት በቅድሚያ መግለጽ ያስፈልጋል። በምክንያት የሚደረጉ ስብሰባዎች አስቸኳይ እና ከትምህርት ዓመቱ ማጠናቀቂያ 10 ቀናት በፊት መደረግ አለበት። ለወላጆች/ሞግዚቶች ስለ ስብሰባው ሠዓት፣ ቀን፣ ቦታ እና ዓላማ/ምክንያቱን የቅድሚያ ማስታወቂያ በስልክ ጥሪ ሊነገር ይችላል። የስልክ ጥሪዎች መመዝገብ አለባቸው እና ስለ ስብሰባው በደብዳቤ ጥሪ ማስከተል ያስፈልጋል።

በተፈጠረው ምክንያት ለሚደረግ ስብሰባ፣ የሰክሽን 504 ቡድን የስብሰባውን ምክንያት/መግለጫ የውሳኔ ሀሳብ በሰክሽን 504 ድረገጽ ላይ መሞላት አለበት። የተሞላው ቅጽ ቅጅ በተማሪው(ዋ) ፋይል በሚስጥር መቀመጥ አለበት።

የዲስፕሊን ጥፋቱ የተከሰተው በተማሪው/ዋ ስንክልና ምክንያት መሆኑን ቡድኑ ካረጋገጠ ተማሪው ወዳለበት የት/ቤት ፕሮግራም (የትምህርት ቦታ) በአስቸኳይ መመለስ ይኖርበ(ባ)ታል። ወላጅ/ሞግዚት እና ሠራተኞች የሚስማሙ ከሆነ የተለየ የትምህርት ቦታ/ሁኔታ እንዲዘጋጅ አስተያየት ሊሰጥ ይቻላል። የትምህርት ቦታ/ሁኔታ ለመለወጥ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ፣ ተማሪው(ዋ) ወዳለ(ች)በት የትምህርት ፕሮግራም (የመማሪያ ሁኔታ/ቦታ) መመለስ ይኖርበ(ባ)ታል።

ይሁንና ግን፣ የዲስፕሊን ጥፋት የተፈጠረው በተማሪው(ዋ) ስንክልና ምክንያት አለመሆኑን ቡድኑ ካረጋገጠ ሌሎች ስንክልና የሌለባቸው ተማሪዎች ላይ በሚወሰደው ዓይነት የጥፋት እርምጃ ተማሪው(ዋ)ን ከት/ቤት ማስወገድ ይቻላል። የዲስፕሊን እርምጃዎች የስቴት ህጎች/ደንቦች በሚፈቅዱት መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋሉ MCPS የተማሪ የስነምግባር መመሪያ/Student Code of Conductስለ መብትና ግዴታ የተማሪ መመሪያ/A Student’s Guide to Rights and Responsibilities እና የMCPS ደንብJGA-RC, ስንክልና ያለበ(ባ)ትን ተማሪ ስለማገድ እና ስለማስወጣት/Suspension and Expulsion of Students with Disabilities

ሰክሽን 504 ዕቅድ ዉስጥ ላሉ ተማሪዎች የትምህርት ድጋፍ የሚሰጠው በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ደንብ መሠረት እኩል ስንክልና ለሌለባቸው ተማሪዎች እንደሚደረገው ይሆናልMCPS የተማሪ ስነምግባር መመሪያ/Student Code of Conduct።

### አደንዛዥ እፆችን ወይም አልኮል ለሚጠቀሙ የሰክሽን 504 እቅድ ተማሪዎች የዲሲፕሊን ሥርዓት

በሰክሽን 504፣ ወቅታዊው ህክምና ያልተደረገለት የአደንዛዥ እፅ ወይም አልኮል ያለአግባብ መጠቀም እንደስንክልና አይቆጠርም። ከአደንዛዥ እፅ ወይም ከአልኮል የተበላሸ አጠቃቀም ቁጥጥር እየተደረገ የተሃድሶ ፕሮግራም በስኬታማነት ያጠናቀቀ(ች) ተማሪ ወደ ጤናማ ሁኔታ ተመልሷል/ተመልሳለች፣ ወይም በወቅቱ የተሐድሶ ፕሮግራም ውስጥ ካለ(ች) በሰክሽን 504 ከለላ ይደረግለ(ላ)ታል።

በተቃራኒው፣ በወቅቱ በአደንዛዥ እፅ ወይም በአልኮል የተበላሸ አጠቃቀም ውስጥ ተዘፍቀው የሚገኙ ተማሪዎች ምክንያታዊ ስብሰባ ወይም ማናቸውም ሌላ የሰክሽን 504 ከለላ ሊደረግላቸው ብቁ አይሆኑም። "አደንዛዥ እፅ ወይም አልኮል የሚጠቀም ወይም ይዞ የተገኘ በማንኛውም ሰከሽን 504 ስንክልና ያለው ተማሪ" ከዚህ ጋር በተገናኘ ምክንያት በወቅቱ አደንዛዥ እፅ/መዳኒት ወይም አልኮል ህገወጥ አጠቃቀም እየተጠቀመ/ች በሚገኝ ስንክልና በሌለበ(ባ)ት ተማሪ ላይ እንደሚደረግ ሁሉ MCPS የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል።

ወቅታዊ ህገወጥ የመድሃኒት አጠቃቀም ማለት በቅርብ ጊዜ የተጀመረ/የተከሰተ ግለሰቡ/ግለሰቧ በቅርቡ የጀመረ(ች) መሆኑን ለማመን የሚያስችል ወይም ከበፊት ጀምሮ(ራ) ሲ(ስት)ጠቀም የነበረ(ች)ና ተያይዞ የመጣ ችግር መሆኑን ነው። አደንዛዥ እፅ ማለት በሰክሽን 202 I እስከ V ላይ በተገለጸው መሠረት ቁጥጥር የሚደረግበት/defined in schedules I through V of Section 202 እፆችን ቁጥጥር ስለማድረግ ደንብ /Controlled Substances Act(21 U.S.C. § 812)

በት/ቤት ንብረት ውስጥ እፅ በሚሸጡ ወይም በሚያዘዋዉሩ/በሚያሰራጩ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲወሰድባቸው ለተፈጠረው ሁኔታ ላስከተለው ምክንያት/መነሾ ስብሰባ ይቀርባሉ። የተማሪው(ዋ) ለሁኔታው መነሾ ምክንያት አለመሆን በቡድኑ ከተረጋገጠ ተማሪው(ዋ) ለሌሎች ስንክልና የሌለባቸው ተማሪዎች በሚሰጣቸው የዲስፕሊን ቅጣት መሠረት እርምጃ ይወሰዳል። ሁኔታው የተከሰተው በተማሪው ስንክልና ምክንያት መሆኑን ቡድኑ ካመነበት፣ ተማሪው በወቅቱ ወደሚማርበት የትምህርት ቤት ፕሮግራም (መማሪያ ስፍራ/ሁኔታ) መመለስ አለበ(ባ)ት።

### መሣሪያ/የጦር መሳሪያ ወደ ት/ቤት ይዘው ስለሚመጡ የሰክሽን 504 እቅድ ተማሪዎች የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

በ18 U.S.C. § 921 (a) ላይ እንደተገለጸው የዲስፕሊን ችግር የተፈጠረው መሣሪያ/የጦር መሣሪያ በሚመለከት ከሆነ በድኑ ከ MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪ ጋር መመካከር እና ከመሣሪያ/ከጦር መሣሪያ ነፃ የሆነ ት/ቤት ደንብ/Gun-Free School Act ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ።

በሰክሽን 504 እቅድ ውስጥ ያለ(ች) ተማሪ ከሽጉጥ/ጠመንጃ ሌላ መሣሪያ ወደ ት/ቤት ይዞ(ዛ) ከመጣ(ች) እና ለዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት ከቀረበ ተማሪው(ዋ) ለዲሲፕሊን ስብሰባ መቅረብ ይኖርበ(ባ)ታል። ምንም በተማሪው ምክንያት የተፈጠረ

የዲሲፕሊን ችግር እንዳልነበረ ቡድኑ ካረጋገጠ ተማሪው(ዋ) ስንክልና የሌለባቸው ተማሪዎች በሚቀጡት ዓይነት የዲሲፕሊን እርምጃ ይስተናገዳል/ትስተናገዳለች። የተፈጠረው ስነምግባር ሁኔታ በተማሪው(ዋ) ስንክልና ምክንያት መሆኑን ቡድኑ ካረጋገጠ ተማሪው(ዋ) በወቅቱ ወደሚ(ምት)ማርበት የት/ቤት ፕሮግራም መመለስ አለበ(ባ)ት (የመማሪያ ሥፍራ/ሁኔታ)

በጥፋት ምክንያት የተደረገ ስብሰባ ይግባኝ

ወላጅ/ሞግዚት ቅጂ ሊሰጣቸው ይገባልበሂደት ላይ ያለ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በጥንቃቄ እንደተጠበቀበጥፋት ምክንያት በሚደረግ ስብሰባ ላይ በራሪ ጽሑፍ ወላጅ/ሞግዚት የተፈጠረውን ሁኔታ ማረጋገጫ ለመቀበል ካልተስማሙ፣ ውሳኔውን በአስተዳደራዊ መዋቅር እንዲታይ፣ በግልግል እንዲታይ፣ እና/ወይም በችሎት እንዲታይ ለመጠየቅ/ይግባኝ ለማለት ይችላሉ። 34 C.F.R. § 104.36. ይመልከቱ ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ/ Montgomery County Board of Education ፖሊሲ/Policy BLC፣ የልዩ ትምህርት ክርክሮችን ስለመዳኘትና ውሳኔ አሰጣጥ መመሪያ ይመልከቱ Procedures for Review and Resolution of Special Education Disputes።

## የተያያዙ አገልግሎቶች

የሰክሽን 504፣ ተማሪዎች ለተገቢ ህዝባዊ የነፃ ትምህርት፣ ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችንም ጨምሮ ባለመብት ናቸው።

ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች የአካል ስንኩልነት ከሌለባቸው ሌሎች ተማሪዎች ጋር እኩል እና አንድ ዓይነት የትምህርት እድል እንደሚኖራቸው ሊረጋገጥላቸው ያስፈልጋል።

ተመሣሣይ አገልግሎቶች ወደ አንድ ተደራሽነት ወዳለው አቅጣጫ ያመራሉ። የሰክሽን 504 ቡድን ተዛማጅ አገልግሎቶች መኖራቸውን ከተጠራጠረ፣ ወይም በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት የሰክሽን 504 እቅድ ከተዛማጅ አገልግሎቶች ጋር እንዲተገበር ከተጠየቀ፣ የሚመለከተው የተዛማጅ አገልግሎት ሠራተኛን ማማከር ያስፈልጋል።

ከተዛማጅ አገልግሎቱ ጋር ግንኙነት ያለው/ያላት የ MCPS ሠራተኛ እንደአስፈላጊነቱ አሠራሩን በተግባር ይገመግማል/ትገመግማለች፣ በሰክሽን 504 እቅድ ዝግጅት ላይ ይሳተፋል/ትሳተፋለች፣ በቀረበው አስተያየት መሠረት ስለመጠቀሚያዎቹ/recommended accommodations አስፈላጊውን ስልጠና ይሰጣል/ትሰጣለች፣ እና ከመምህራን ጋር ተማሪው(ዋ) በት/ቤት አካባቢ መገልገለል ስለሚችልበት/ስለምትችልበት ሁኔታ እና በት/ቤት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ስለሚ(ት)ችልበት ሁኔታ ሁሉ ይመካከራል/ይነጋገራል።

## የወላጅ/ሞግዚት ትብብር እና ተሳትፎ

ወላጆች/ሞግዚቶች በቤት-ት/ቤት አጋርነት አስፈላጊ አካል ናቸው። በሰክሽን 504 ሂደት ላይ ወላጆች/ሞግዚቶች ተባባሪ አጋሮች መደረግ አለባቸው። የት/ቤት ሥራ ባልደረባ ወላጆችን/ሞግዚቶችን ለመድረስ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም በዚህ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማበረታታት በተነሳሽነት መትጋት አለበ(ባ)ት።

በሰክሽን 504 የትምህርት ሂደት ወላጆች/ሞግዚቶች የመሳተፍ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን የሚረጋገጥበት አሠራር መስፈን እንዳለበት ህጉ ይደነግጋል።

በሰክሽን 504 መሠረት፣ ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ህጉ የሚጠይቀውን መስፈርት ማሟላት እንደሚችል/እንደምትችል በተሰማቸው ጊዜ የሰክሽን 504 ብቃትን ለምልመላ ስብሰባ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አላቸው። ሰክሽን 504 በመጀመሪያው ደረጃ/መነሻው ላይ ለሚደረገው ግምገማ የወላጆች እውቀትና ስምምነት ብቻ ያስፈልጋል። ት/ቤቶች ማናቸውንም በወላጆች/ሞግዚቶች አማካይነት የቀረቡላቸውን መረጃ/ስጋት/ኢንፎርሜሽን ላይ ለመወያየትና ለመገምገም ለ 504 ቡድን ስብሰባ ቀጠሮ አስይዘው መጥራት አለባቸው። ይኼኛው ስብሰባ ተማሪው(ዋ) ምን አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደገጠሙ(ሚ)ት ሀሳቦችን ለማንሸራሸር እድል የሚሰጥ ነው።

ለሰክሽን 504 ከለላ ብቃት ላላቸው/መስፈርት ለሚያሟሉ ተማሪዎች በመተባበር ስልቶችን መለየት እና እቅድ ማዘጋጀት ከሚፈለገው ውጤት ላይ ለመድረስ የባለቤትነት እና የኃላፊነት ስሜት ያጎናጽፋል።

የሰክሽን 504 ቡድን ተማሪው(ዋ) ለሰክሽን 504 ብቁ መሆን አለመሆኑ(ኗ)ን ይወስናል። የሰክሽን 504 ቡድን ግምገማ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል፣ እና ከወላጅ/ሞግዚት ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል (ይመልከቱ፡- MCPS ቅጽ 336-31፣ ግምገማ እንዲደረግ ፈቃድ መስጫ )

የሰክሽን 504 እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ወላጆችን/ሞግዚቶችን መጨመር በሂደቱ ላይ በጣም አስፈላጊ እርምጃ ነው። ወላጆች/ሞግዚቶች እቅዱን በማዘጋጀቱ ላይ መሣተፍ አለባቸው ወይም አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት መንገድ መመቻቸት አለበት። ቡድኑ እቅድ ሲዘረጋና ተገቢ የሆነ መገልገያ/መጠቀሚያዎች/accommodations እና ስልቶችን ሲያዘጋጅ እንደየአስፈላጊነቱ የወላጆችን/የሞግዚቶችን ሃሳቦቻቸውንና አስተያየቶችን መቀበልና ግንዛቤ መስጠት ይኖርበታል።

በእቅዱ ላይ ወይም በማናቸውም የሂደት ደረጃ ወላጆች/ሞግዚቶች ካልተስማሙ ቡድኑ ጉዳዩን የማስፈጸም አማራጮችን ለወላጆች ማረጋገጥ እና ያልተግባቡበትን ጉዳይ መጀመሪያ በት/ቤት ደረጃ መፍትሔ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል። አስፈላጊ ከሆነ፣ ከMCPS የሰክሽን 504 አስተባባሪ የውሳኔ አስፈጻሚ እና ትግበራ ን/ክፍል ተጨማሪ ድጋፍና ተሳትፎ ለማግኘት ይቻላል። የሰክሽን 504 በራሪ ጽሑፎች/መመሪያዎች፡- የወላጆች/የሞግዚቶች መመሪያ ለሰክሽን 504 የ1973 የተሐድሶ ህግ /A Parent's/Guardian's Guide to Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973 እና Due Process Safeguards/የፍርድ ሂደት ማስከበሪያዎች መረጃ/Information ከ504 ቡድን ስብሰባ አስቀድሞ ለወላጆች/ለሞግዚቶች መሰጠት አለበት።

## ለሰክሽን 504 ተማሪዎች የሚገባ መብት አፈጻጸም ሥርዓት

ከዚህ የሚከተለው በፌደራል ህግ  እና  በ MCPS ደንብ ACG-RB፣ በተሐድሶ ደንብ 1973 መሠረት መስፈርት ለሚያሟሉ የሰክሽን 504 ተማሪዎች ተስማሚ መገልገያዎችን እና ማሻሻያ ለውጦችን/Reasonable Accommodations and Modifications for Students Eligible Under Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973 መሰረት በሰክሽን 504 ለታቀፉ ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች የተሰጡ መብቶች አጭር መግለጫ ነው።

- በስንክልና ምክንያት አድሎ/ተፅእኖ ሳይደረግባቸው በህዝባዊ የትምህርት ፕሮግራሞች የመሣተፍ እና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት፤
- ተማሪው(ዋ)ን የሚመለከቱ ስለማንነት፣ የግምገማ ውጤት፣ ዳግም ግምገማ፣ ወይም የምደባ/የፕሮግራም ውሳኔዎችን የማግኘት መብት፣
- ተማሪው/ተማሪዋ ተገቢውን የህዝባዊ ትምህርት በነፃ የማግኘት መብት። ይህ እስከ መጨረሻው አግባብ እስከሆነ ድረስ ጉድለት ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር የመማርን መብት ያጠቃልላል፤
- በት/ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ የት/ቤት ፕሮግራሞች እና ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ስንክልና የሌለባቸው ተማሪዎች የሚያገኙትን እኩል እድል የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።
- ከተለያዩ ምንጮች በሚገኙ መረጃዎች እና ተማሪው(ዋ) ስለሚያስፈልገው/ስለሚያስፈልጋት ነገሮች በሚያውቁ ሰዎች  እና ለግምገማ የቀረቡ መረጃዎችን ተንተርሶ ስለሚሰጡ ውሳኔዎች ትርጉም/ትንተና፣ የምደባ/የፕሮግራም አማራጮች የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ እና የምደባ/የፕሮግራም ውሳኔዎችን የማወቅ መብት፤
- በ MCPS ደንብ JOA-RA መሠረት የተማሪ የትምህርት ሪኮርዶች/መረጃዎችን የመመርመር፣ እና ኮፒ/ቅጂ የማግኘት መብት የተማሪ ሪኮርዶች/መረጃዎች፣ እና
- ስለ ተማሪው(ዋ) ማንነት መለያ/identification፣ ግምገማ፣ ዳግም ግምገማ፣ ወይም የምደባ/ፕሮግራም የትኛውንም ውሳኔ በሚመለከት ወላጅ/ሞግዚት ካላረካቸው በጉዳዮቹ ላይ የመፍትሔ ውሳኔ የመጠየቅ መብት አላቸው።

እነዚህ መብቶች በ MCPS ሰክሽን 504 የመግለጫ መጽሔት/brochures ላይ በሙሉ በሙሉ ተብራርተዋልበ RACU Section 504 website/ድረገጽ ላይ በሚገኘዉ። የ MCPS ሰክሽን 504 የመግለጫ መጽሔት/brochures ለማናቸውም የሰክሽን 504 ቡድን ስብሰባ ወቅት ለወላጆች ሞግዚቶች መላክ አለበት ወይም በስብሰባ ወቅት መሰጠት አለበት ካልሆነም በጠየቁ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

ለተማሪ የሰክሽን 504 እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት  ወላጅ/ሞግዚት የ504 እቅዱ ሲዘረጋ መሳተፋቸውንና የእቅዱን/ፕላን ቅጂ/ኮፒ ማግኘታቸውን በማረጋገጥ መፈረም ይኖርባቸዋል የፍርድ ሂደት ማስከበሪያ መረጃ።

## ለተጨማሪ መጠቀሚያዎች/RESOURCES የሚቀርብ ጥያቄ

ሰክሽን 504 ለመተግበር/ለማስፈጸም ተጨማሪ መጠቀሚያዎች/Resources ለቀረበው ጥያቄ (በወቅቱ በት/ቤት ውስጥ የለም)

ለመደበኛ ትምህርት ተማሪ ሰክሽን 504 እቅድ ለመተግበር መጠቀሚያ/Accommodations እና ጣልቃ የመግባት ስልት በተለምዶ በመደበኛ የመማሪያ ክፍል መምህራን ላይ የሚወድቅ ነገር ነው። በሰክሽን 504 ቡድን መወሰን ያለበት ለተማሪው(ዋ) የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ዓይነት ማቴሪያል፣ ቴክኖሎጂ፣ ወይም በወቅቱ በት/ቤቱ ውስጥ የሌሉ ባለሞያ ሠራተኞች፣ ከዚያ ቀጥሎ ርእሰ መምህሩ(ሯ) ወይም ተወካይ ከሰክሽን 504 አስተባባሪ ጋር እና ከማዕከል ቢሮ የሥራ ባልደረቦች ጋር ተጨማሪ መገልገያዎችን/resources ለማግኘት ይሰራሉ።

## አጭር መዝገበ ቃላት

### ስንክልና

አካለ ስንኩል ማለትበአካለ ስንክልና የሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ/ Americans with Disabilities Act መሰረት (ADA) (a) የአንድን ግለሰብ አንድ ወይም የሚበልጥ ዋና የህይወት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ አካላዊ ወይም የአእምሮ ድክመትን የመሳሰለ፤ (b) እንደዚህ ዓይነት ድክመት/ስንኩልነት ሪኮርድ/መረጃ ወይም (c) እንደዚህ ዓይነት ስንክልና አለበ(ባ)ት ተብሎ የታሰበ(ች) ማለት ነዉ።

### እኩል የማግኘት እድል

ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ በሕብረተሰብ ኤጀንሲ በሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የትምህርት መርጃ፣ ጥቅማጥቅሞች፣ ወይም አገልግሎቶችን በእኩልነት የመሣተፍ/የመጠቀም እድል።

### ግምገማ

ተማሪው(ዋ) በሰክሽን 504 ላይ ስለ ስንክልና ትርጓሜ የተገለጸውን መስፈርቶች እንደሚያሟላ/እንደማያሟላና፣ስለዚህም፣ ሰክሽን 504 እቅድ ላይ ለመግባት መቻሉ/ሏን ግምገማዉ ይወስናል። ሰክሽን 504 ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ የሚገመቱ ተማሪዎች ምንም ዓይነት እርምጃ ከመወሰዱ አስቀድሞ ለተማሪው(ዋ) የመነሻ ምደባ ከመሰጠቱ በፊት እና ስለምደባ ከባድ ለውጥ ከመደረጉ አስቀድሞ ግምገማ መካሄድ አለበት። የግምገማው መረጃ/data የሚያካትተው (በዚህ አይወሰንም)፣ ይፋ እና ይፋዊ ያልሆኑ ቴስት የተደረገባቸው መሣሪያዎች፣ አጠቃላይ እውቀትና የተገኘው ውጤቶች፣ የመምህር አስተያየቶች፣ የአካል ወይም የጤና ምርመራ ሪፖርቶች፣ የተማሪው(ዋ) ውጤቶች፣ በየጊዜው እርምጃ/ለውጥ ሪፖርቶች፣ የወላጅ/ሞግዚት ያስተዋሉት ሁኔታ፣ግለሰባዊ ሪኮርዶች፣ እና የስነምግባር ግምገማዎችን ነው።

### ተገቢ ነፃ ህዝባዊ ትምህርት

ለሰክሽን 504 ዓላማ፣ "አግባብነት ያለው ነፃ ህዝባዊ ትምህርት" (FAPE) የሚያመለክተው ስንክልና ያለበ(ባ)ት ግለሰብ የትምህርት ፍላጎትን ልዩ ሁኔታ መሠረት ተደርጎ የተዘጋጀ መደበኛ ወይም ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅነት ያላቸው ድጋፎችንና አገልግሎቶችን ስንክልና ለሌላቸው ተማሪዎች በሚሰጣቸው መጠን እኩል/ የተመጣጠነ፣ የሰክሽን 504 መመሪያዎችን በጥብቅ የተከተለ እና ከትምህርት ቦታ ሁኔታ ጋር የተገናኘ፣ ግምገማ እና ምደባ ሂደት ሥነ ሥርዓት የጠበቀ። እባክዎን ይኼኛው ከ በአካለስንኩልነት የሚኖሩ አሜሪካውያን የትምህርት ደንብ (IDEA) የተለየ ደረጃ የጠበቀ ነገር መሆኑን፣ ቢሆንም፣ ከ FAPE ተፈላጊ መስፈርቶች ከ IDEA ጋር የሚጣጣም ከሆነ በሰክሽን 504 ከ FAPE ተፈላጊ መስፈርቶችም ጋር ይጣጣማል። 34 C.F.R. § 104.33

### በጣም አነስተኛ ገደብ ያለው አካባቢ

ስንክልና ላለበ(ባ)ት ተማሪ የሚያስፈልጉትን ሁሉ በማሟላት እስከመጨረሻው ጣራ ድረስ በሚስማማው/ት ሁኔታ ተመቻቶለ(ላ)ት ስንክልና ከሌለባቸው እኩያዎች ተማሪዎች ጋር አንድ ላይ/አብረው ይማራሉ። ስንክልና ላለበ(ባ)ት ተማሪ የሚቀርቡት ልዩ የትምህርት መርጃዎች እና አገልግሎቶች በመደበኛ የትምህርት ቦታዎች የማይሟሉ ካልሆነ በስተቀር፣ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ ወደ መደበኛ የትምህርት ቦታ ገብቶ(ታ) መማር አለበ(ባ)ት። 34 C.F.R. § 104.34.

### ዋና የህይወት እንቅስቃሴ

"ዋና የህይወት እንቅስቃሴ "የሚለው ሃረግ በዚህ ሳይወሰን የሚከተሉትን ያካትታል፦

1. ራስን መንከባከብ፣ በእጅ/በጉልበት የሚሠሩ ሥራዎችን መሥራት፣ ማየት፣ መስማት/ማዳመጥ፣ መመገብ/መብላት፣ መተኛት፣ መራመድ፣ መቆም፣ መቀመጥ፣ እጅ/እግር ዘርግቶ መድረስ፣ እቃ/የሆነ ነገር ወደላይ ማንሳት፣ ማጎንበስ፣ መናገር፣ መተንፈስ፣ መማር፣ ማንበብ፣ ትኩረት ማድረግ፣ ማሰብ፣ መፃፍ፣ መገናኘት፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ እና መሥራት፣ እና
2. ዋና ዋና የሰውነት/አካላዊ ሥራዎች፣ በሽታን የመከላከል/የመቋቋም አቅም/ሥርዓት፣ ስሜትን የመለየት ልዩ የሰውነት ክፍሎች/ ኦርጋኖች እና የሰውነት ቆዳ/ገላ፣ ጤናማ የህዋስ/የሴል እድገት፣ እና የምግብ ውህደት፣ የሽንት መፀዳጃ፣ አንጀት፣ የሽንት ፊኛ፣ የነርቭ ህዋስ፣ ጭንቅላት፣ የመተንፈሻ አካላት፣ የደም ዝውውር፣ የልብ፣ ኢንዶክራይን እጢዎች፣ ደም፣ በደም ስር ውስጥ ያለ ፈሳሽ ነገር፣ ጡንቻዎች፣ እና የመዋለጃ አከላት የመሳሰሉት ናቸው። የዋና ሰውነት አካል ስራ በሰውነት ስርዓት ውስጥ ያለ የአንድን ኦርጋን/የሰውነት ክፍል ስራን ያካትታል። 34 C.F.R. § 104.3 and 29 C.F.R. § 1630.2

### ማቃለያ እርምጃዎች

"የማቃለያ እርምጃዎች" የሚለው ሃረግ በዚህ ሳይወሰን፣ የሚከተለውን ያካትታል፦

1. መድኃኒት፣ የህክምና መዳሃኒቶችና መሣሪዎች፣ መገልገያ መሣሪያዎች/እቃዎች፣ አጥርቶ ለማየት የሚረዱ መሣሪያዎች (አጉልቶ የሚያሳይ፣ አጥርቶ የሚያሳይ፣ ወይም ሌላ የማየትን ችግር የሚያቃልል፣ ነገር ግን መደበኛውን ዓይነት የዓይን መነፅር ወይም ኮንታክት ሌንስ አይጨምርም)፣ ሰው ሠራሽ የአካል ምትክ ቅጥያዎችንና የተገጠሙ መሣሪያዎችን ጨምሮ፣ለመስማት የሚረዱ መሣሪያዎች፣ በቀዶ ጥገና ጆሮ ውስጥ ገብቶ ለመስማት የሚረዳ ወይም ሌሎች በጆሮ ገብቶ ሁል ጊዜ ለመስማት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣ የመንቀሳቀሻ መሣሪያዎች፣ የኦክስጅን መሣቢያ/ ማስገቢያ መሣሪያና አብረው ያሉ መገልገያዎች/supplies፤
2. አጋዥ ቴክኖሎጂ መጠቀም፤
3. በዚህ ደንብ ላይ የተገለጹ/የተብራሩ በተገቢ ሁኔታ ማሻሻያ ለውጥ የተደረገባቸው ተጨማሪ መርጃዎችና አገልግሎቶች፦
4. የተለመደ ባህሪይ ወይም ተስማሚ የነርቭ ህዋስ ማሻሻያዎች/ ለዉጦች፤ ወይም
5. የስነልቦና ህክምና፣ የስነምግባር ህክምና፣ የአካል ህክምና (Psychotherapy, behavioral therapy, or physical therapy)

### አድሎዎን (አድሎአዊ አሠራርን) ስለማስቀረት

በሰክሽን 504 መሠረት አድሎ መደረግ እንደሌለበት በሚከተለው አይነት ተገልጿል። "በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ማንኛውም ስለ ስንክልና መስፈርቶችን አሟልቶ የተገኘ ሰው፣ አካለ ስንኩል በመሆኑ(ኗ) ምክንያት ብቻ ከመሳተፍ አይገለልም/አትገለልም፣ ከማናቸውም ጥቅማጥቅሞች አይከለከለም/አትከለከልም፣ ወይም በማናቸውም ፕሮግራም ላይ አድሎ አይደረግበ(ባ)ትም"።

በሰክሽን 504፣ በህዝብ ኤጀንሲዎች አማካይነት የፋይናንስ ድጋፍ በሚደረግላቸው ፕሮግራሞች፣ እንቅስቃሴዎች፣ እና አገልግሎቶች ሁሉ እኩል የማግኘት እድል ኖሯቸው ተጠቃሚ ለመሆን መቻላቸውን ምንም አድሎ እንዳልተደረገባቸው ተጠቃሚዎች ማረጋገጥ አለባቸው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ከሰክሽን 504 ጋር የሚጣጣም የፀረ-መድሎ ፖሊሲ መስርቷል። ፖሊሲ ACA ይመልከቱ፦ አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት/ፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል።

## አጭር መዝገበ ቃላት

**የዜጎች መብት ጽ/ቤት**

በዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት የዜጎች መብት ጽ/ቤት  ሰክሽን 504 ያስፈጽማል እናም ቅሬታዎች ካሉ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ምርመራ ያካሄዳል።

**ወላጅ**

በሰክሽን 504 መሠረት "ወላጅ" ማለት ተፈጥሮአዊ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ ወይም ሞግዚት፣ አሳዳጊ ወላጅ፣ እንደ ወላጅ የተተካ (ለምሳሌ፡- ልጁ አብሮት የሚኖር አያት) ወይም አንድ በህጋዊ ሁኔታ ለልጁ/ለልጅቱ ኃላፊነት ያለው ሰው።

**የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልና**

1. ማናቸውም የአካል ጤንነት ቀውስ ወይም የመዛባት ሁኔታ፣ የሰውነት ቅርፅ መበላሸት፣ ወይም ከሰውነት ክፍል አንድ ወይም የበለጠ የአካል ጉዳት ያለበ(ባ)ት፣ እንደ ነርቭ በሽታ፣ የጡንቻ መላላት፣ ልዩ የስሜት ህዋሳት መጎዳት፣ የመተንፈሻ አካል (የመነጋገሪያ አካልን ጨምሮ)፣ የልብ ህመም፣ የመዋለጃ ብልቶች፣ የምግብ ውህደት ችግር፣ የሽንት መሽኛ/መፀዳጃ፣ በሽታን መከላከል/መቋቋም፣ የደም ዝውውር፣ የደም ህዋሳት፣ በደምስር ውስጥ የሚተላለፉ ፈሳሽ ሆርሞኖች፣ ቆዳ፣ እና ኦንዶክራይን ሆርሞን/ዕጢ፣ ወይም
2. ማናቸውም የአእምሮ ወይም የስነልቦና ጤንነት መዛባት የአእምሮ ድክመት፣ የአእምሮ ቀውስ፣ ስሜታዊነት ወይም የአእምሮ በሽታ፣ የተለየ ለመማር ያለመቻል።

አካላዊ ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንክልና የሚለው ቃል (በዚህ አይወሰንም) የሚያካትተው፣ ተላላፊ እና የማይተላለፉ በሽታዎች እና ሁኔታዎች  እንደ የሰውነት መገጣጠሚያ ክፍሎች መዛባት የማየት ችግር፣ መናገር እና መስማት/ማዳመጥ አለመቻል፣ ዘላቂ የሆነ የአእምሮ መበላሸት፣ የሚጥል በሽታ/epilepsy፣ የጡንቻዎች መዳከም፣የቲሹዎች እብጠት/multiple sclerosis፣ ካንሰር፣ የልብ በሽታ፣ የስኳር በሽታ፣ የአእምሮ ድክመት፣ ስሜታዊነት/ግንፍልነት፣ ከአንጎል መጎዳት የሚመጣ ፊደላትን መለየትና ማንበብ አለመቻል/dyslexia እና ሌላ የተለየ የማወቅ/የመማር ድክመት፣ ትኩረት ማጣት ቅብጥብጥነት፣  ኤች አይ ቪ ቫይረስ፣ (አመላካች ወይም ምልክት ያልታየ)፣ የሳንባ በሽታ፣ የአደንዛዥ እፅ ሱሰኛነት(በመጠቀም ላይ ያለ/ች)፣ እና የአልኮል ሱሰኛነት። 34 C.F.R. § 104.3

**የሴክሽን 504 ፕላን Section 504 Plan**

ሰክሽን 504 እቅድ ማለት በሰክሽን 504 ቡድን አማካይነት በጽሑፍ የተዘጋጀ ተስማሚ/ተገቢ ነፃ ህዝባዊ ትምህርት፣ ለተማሪው/ለተማሪዋ ትምህርት አስፈላጊ ሆነው ዲዛይን የተደረጉ መጠቀሚያዎች/accommodations እና ተዛማጅ መርጃዎች እና አገልግሎቶችን ለመስጠት የተዘጋጀ ሠነድ ነው።

**በከፍተኛ ደረጃ ይገድባል**

"በከፍተኛ ደረጃ የሚገታ" ADA እና ADAAA አገላለጽ ላይ እንደተፈቀደው የተቻለውን ያክል በስፋት ሽፋን ለመስጠት እንደሆነ በስፋት ተብራርቷል። (ይህ በ ADAAA የተመሠረተው ደረጃ በሰክሽን 504 ተካቷል)። የአእምሮ ወይም የአካል ድክመት  በዚህ ክፍል ላይ እንደተገለጸው ስንክልና ከሌለባቸው እኩያሞች ጋር ሲወዳደር የግለሰብን ዋና ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎች የማከናወን ችሎታ በከፍተኛ ደረጃ የሚገድብ ስንክልና፣ ሁኔታዎችን ለማሻሻል የማቅለያ እርምጃ (ተራ የዓይን መነፅር ወይም ኮንታክት ሌንስ ሳይጨምር) የሚያመጣውን ለዉጥ ሳያገናዝብ ማለት ነዉ። ስንክልና የህይወት እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጎዳ/እንደሚገድብ እስከሚታሰብ የግድ ዋና የህይወት እንቅስቃሴችን በከፍተኛ ደረጃ መከልከል/መገደብ አይኖርበትም። አንድን ዋና የህይወት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ ስንክልና መሆኑን ለመቀበል/ለመወሰን ሌላውንም ዓይነት ዋና የህይወት እንቅስቃሴ እስከሚጎዳ መጠበቅ የለበትም። በየጊዜው የሚነሳ እና ጋብ የሚል የህይወት ዋና እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ደረጃ የሚገድብ ከሆነ ስንክልና ነው።

## የ MCPS ሰክሽን 504 ቅጾች

**የሰክሽን 504 ግምገማ፣ የሰክሽን 504 እቅድ፣ ለሆነ ነገር ምክንያታዊ ስብሰባ፣ እና ከሰክሽን 504 የሚላኩ ደብዳቤዎች በሙሉ መሞላት ያለባቸው የሰክሽን 504 ፕላትፎርም-ድረገጽ ላይ ነው። በተጨማሪውም የሚከተሉትን የ MCPS ቅጾች እንደ አስፈላጊነታቸው መጠቀም ይቻላል፡-**

MCPS ቅጽ 270-2A ለት/ቤት ሳይኮሎጂስት ሰክሽን 504 በትኩረት የመከታተል ችግርን ለመገምገም ኃላፊነት-ፈቃድ መስጫ ቅጽ

MCPS ቅጽ 270-2C ሰክሽን 504 የመሻሻል/ለውጥ እና የመጠቀሚያ/Accommodation ግምገማ ሠነድ (በሚስጥር የሚያዝ)

MCPS ቅጽ 270-2D የሰክሽን 504 እቅድ ስርጭት (በሚስጥር የሚያዝ)

የ MCPS ቅጽ 272-9 የመምህር ማስተላለፊያ

MCPS ቅጽ 272-7 የኤለመንተሪ መምህር ሪፖርት

የ MCPS ቅጽ 272-8 የሁለተኛ ደረጃ መምህር ሪፖርት

የ MCPS ቅጽ 336-31 ለግምገማ ፍቃድ መስጠት (በሚስጥር የሚያዝ)

የ MCPS ቅጽ 336-32 በሚስጥር የሚያዝ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመለዋወጥ/ለመስጠት ፍቃድ መስጫ

የ MCPS ቅጽ 336-68 ቡድኑ የተቀበለው የውጭ ሪፖርት

## የ MCPS ደንብ እና ደጋፊ ሠነዶች

MCPS ደንብ ACG-RB, የተሐድሶ ደንብ 1973ሰክሽን 504 ለመሳተፍ ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ መጠቀሚያ/Accommodations እና ማሻሻያ ለውጥ ስለማድረግ

የ MCPS ደንብ JGA-RC, ስንክልና ያለባቸውን ተማሪዎች ስለማገድና ማባረር/ማሰናበት

የተሐድሶ ደንብ 1973 ስለ ሰክሽን 504 የወላጅ/ሞግዚት መመሪያ **የሚገኘው በ** RACU Section 504 website**/ድረገጽ**

በሒደት ላይ ያለ መረጃ በጥንቃቄ መጠበቅ/የውሳኔ ሂደት ማስከበሪያ መረጃ፡- ሰክሽን 504 የተሐድሶ ደንብ 1973 **መጽሔት/**brochure, RACU ሰክሽን 504 ድረገጽ ላይ ይገኛል።

## የሰክሽን 504 መገልገያዎች/RESOURCES

በዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ በኤለመንተሪ እና በሁለተኛ ደረጃ የህዝብ ት/ቤቶች ስለ ሰክሽን 504 የወላጅ እና አስተማሪ መገልገያ/ Resource መመሪያ

ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ ስለ ሰክሽን 504 እና ስንክልና ስላለባቸው ልጆች ትምህርት በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

የዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት፣ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ በስንክልና ምክንያት የሚደረግ አድሎ ማድረግ

ዩ. ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት፣ በ OCR የቅሬታ አፈጻጸም ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

# የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
# MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፤ ጎሳ፤ ቀለም፤ የዘር ሃረግ፤ የብሔር ማንነት፤ ኃይማኖት፤ የስደተኝነት ሁኔታ፤ ጾታ፤ ስነ-ጾታ፤ የጾታ ማንነት (gender identity)፤ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፤ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፤ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፤ የጋብቻ ሁኔታ፤ እድሜ፤ ድህነት፤ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፤ ቋንቋ፤ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፤ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፤ ፍትሕ፤ አብሮነት፤ሁሉን አቀፍነትን፤ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፤ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡-ጥላቻ፤ ሁከት፤ ደንታቢስነት፤ ወከባ፤ ማስፈራራት፤ ማሸማቀቅ፤ ንቀት፤ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፤ ፍትህ፤ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፤ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፤ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፤ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | ት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት Office of School Administration<br>የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክፍል Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>301-279-3444<br>OSSI-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ክትትል፤ ቅሬታ/ስሞታ፤ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፤ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 301-517-5864 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፤ ስልክ፡- 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፤ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የህዝብ ኢንፎርሜሽን እና የድረ-ገጽ አገልግሎት ክፍልን በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837, 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ), ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም Interpreting_Services@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

ሕትመት፡- Department of Materials Management for the Resolution and Compliance Unit
ትርጉም፡- በቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ክፍል • የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት
Language Assistance Services Unit • Office of Communications
0207.18ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 11/17 • NP